# የአሲምባ ውይይት መድረክ
# ለፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ ራዲዮ
# ልዩ የርዳታ ዝግጅት ያደርጋል

ቅዳሜ ጥር 12 ቀን 2010

Saturday January 20, 2018

---

ቅዳሜ ጥር 12 ቀን 2010 January 20, 2018

**የፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነት ድምፅ ራዲዮ ጣቢያን እንርዳ፡-**

የኢሲምባ የፓለቶክ ውይይት መድረክ ቅዳሜ ጥር 12 ቀን 2010 (እኤአ 01/20/2018) ከቀኑ 2:00 የዋሽንግተን ዲሲ ሰዓት አቆጣጠር ጀምሮ የገንዘብ እርዳታ ለማሰባሰብ በምናደርገው ዝግጅት ላይ በውጭ ያላችሁ አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን እንድትገኙልን በማክበር እንጋብዛለን።

የፍኖተ ራዲዮ ጣቢያ ለኢትዮጵያውያን፣ በኢትዮጵያውያን፣ ስለኢትዮጵያውያን የተቋቋመና፤ ከተመሠረተበትም ጊዜ አንስቶ በሀገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን እርዳታ ብቻ ፕሮግራሙን የቀጠለ ዕውነተኛ ኢትዮጵያዊ አማራጭ ራዲዮ ስለሆነ የሀገር ወዳዶችን እርዳታ ይሻልና ሁላችንም እንረባረብ። የፍኖተ ራዲዮ በ ሳተላይ የሚተላለፍ ሲሆን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የኢትተርኔት ቴሊቪዥን መጀመሩ ሲታወቅ ይህም ዝግጅት ወደ ሀገር ቤት እንዲገባ የሚያግደው አቅም ብቻ ስለሆነ የሀገር ወዳዶችን እርዳታ ይሻል።

በተለይም በአሁኑ ጊዜ በየአዝጣጫው የተነሳሳው ሕዝባዊ አመጽ በኢትዮጵያዊነት ጥላ ሥር ተሰባስቦ አድጎ ልክ እደዚያ ትውልድ ጊዜ እንቅስቃሴው በሀገራዊ ደረጃ እንዲደግ የምንፈልግ ከሆነና ከሁሉም በላይ አቅጣጫውን ስቶ በዘረኝነት ተተብትቦ አደጋ ሊያደርስ የሚችል ኃይል ሆኖ እንዲወጣ የሚገፋፉትንና ለክሽፈቱ ሌት ተቀን የሚሠሩ አሰፍስፈው የሚወራጩትን የዘረኞች መንጋ ሴራቸውን በትምህርት ለማክሸፍ ይህ ራዲዮ ጣቢያ ሊጫወት የሚችለውን ሚና ከዝግጅቱ የምንገነዘብ ሁላ ይህን ሕዝባዊ አመጽ ኢትዮጵያዊ መልክና ቅርጽ እንዲይዝ የሚያስችል ጉልበትና ማስተማሪያ አስተማማኝ ኢትዮጵያዊ ራዲዮ ጣቢያችንን ካለማመንታት ተሰባስበን እንርዳ።

በዚህ ዕለት ከሬዲዮ ጣቢያው፣ ከፍኖተ ርዕይ የዝግጅት ክፍልና ከኢሕአፓ የአመራር አባላት በመድረካችን በመገኘት ስለ ራዲዮ ጣቢያውና ፍኖተ ርዕይ ገለጻ ስለሚያደርጉ፣ በመድረካችን በመገኘት ያላችሁን ጥያቄ በማቅረብ ወደፊትም ራዲዮኑ የርዕዩ (ቴሉቪዥኑ) ክንፍ እንዴት ሊጠናከር እደሚቻል ጠቃሚ ሃሳብ ልታቀርቡ የምችሉበት ሁናቴ ያመቻቸን ሲሆን፣ ከራዲዮ ዝግጅት ክፍልሉ ጋርም በመተባበር ለዕለቱ ልዮ ዝግጅት ይዘን የምንቀርብ መሆኑን እናስታውቃለን።

የአሲምባ የፓልቶክ የውይይት መድረክ በየሳምንቱ ቅዳሜ በዋሺንግተን ዲሲ ሰዓት አቆጣጠር ከቀኑ 2 ሰዓት ጀምሮ የሚከፈትና እነሆ ለለፉት 11 ዓመታት የሀገራችንን ፖለቲካ ሁኔታ በሚመለከት የተለያዩ በሳል ሀሳቦች የሚንሸረሸሩበት ዴሞክራሲያዊ የውይይት መድረክ ነው።

የአሲምባ ውይይት መድረክ